Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

MCPS ቅጽ 339-1
ሜይ 2020

# ስለ ግለሰብ የምክር አገልግሎት የስምምነት መግለጫ

Office of Student and Family Support and Engagement
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland 20850
**የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ ሰጪ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት**
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS Maryland
CLEAR FORM

የተማሪው/ዋ ስም ______________________ የተወለደ(ች)በት ቀን_____/_____/______ የ MCPS መታወቂያ # __________

የት/ቤት ስ -- Choose One -- ______________________ የክፍል ደረጃ ________

የወላጅ/አሳዳጊ ስም ______________________ የስልክ ቁጥር______-______-_______

ዓላማ ______________________ አገልግሎቱ የሚቆይበት ጊዜ ______________________ የእያንዳንዱ ክፍለጊዜ ርዝመት ________

ከወላጅ(ጆች) ወይም ሞግዚት(ቶች) በሚሰጥ ፈቃድ ለተማሪዎች የትምህርት ቤት ካውንስለር፣ ሳይኮሎጂስት፣ ወይም ሶሻል ዎርከር በመደበኛነት ወይም በተከታታይ ክፍለጊዜ የግል ካውንስሊንግ ይሰጣሉ። እነዚህ የምክር አገልግሎት ክፍለ ጊዜዎች የተቀረጹት ተማሪዎች በአካዳሚያዊ/በትምህርታቸው እና በማህበራዊ ህይወታቸው የበለጠ ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዱ ክህሎቶችን ለማስተማር ነው። የግል ካውንስሊንግ ጊዜዎችን በመጠቀም በርካታ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ሥራዎቻቸውን፣ ትኩረት፣ እና ስለትምህርት ቤት የሚኖራቸውን ዝንባሌ ሊያሻሽሉ ይችላሉ። ለእነዚህ የካውንስሊንግ ክፍለጊዚዎች የተዘጋጁት ራስን-የመርዳት ዘይቤዎች በአብዛኛው አስቸጋሪ ሁኔታን የመቋቋም ስልቶች፣ ጭንቀትን/ውጥረትን መቋቋም፣ ፕሮብሌም መፍታት፣ እና ማህበራዊ ክህሎቶችን ያካትታሉ። እነዚህ ክፍለ ጊዜያቶች እርስዎ ለተማሪው/ዋ ከት/ቤት ውጪ ሊያዘጋጁ የሚችሉትን የምክር አገልግሎት ለመተካት የታሰቡ አይደሉም። እባክዎ ተማሪው(ዋ) ለሚያደርገው-ለምታደርገው ለእያንዳንዱ የካውንስለር ጉብኝት ማድረግ/አለማድረግ ይህ ስምምነት አስፈላጊ እንደማይሆን እና ስምምነቱ አስፈላጊ የሚሆነው በመደበኛነት ወይም በተከታታይ ለሚደረግ የግል ካውንስሊንግ ክፍለጊዜዎች ብቻ ይሆናል። ይሄ በተለይም የኮርሶችን ክፍለጊዜ ወይም የኮሌጅ እና ሙያዊ እቅድን በሚመለከት የሚደረጉ ጉብኝቶችን አይጨምርም።

ልዩ ሁኔታዎች ካልሆኑ በስተቀር (ለምሳሌ፡- አንድ ተማሪ ለራሱ(ሷ)፣ ለእነርሱ፣ ለሌሎች ወይም ለንብረት የሚያሰጋ-የምታሰጋ ካልሆነ በስተቀር) በተለይም በካውንስሊንግ ክፍለጊዜ ከተማሪ የተሰጠ መረጃ ለማንም ይፋ አይደረገም። ለ MCPS አስተዳደር ሃላፊዎች ወይም ስለ ተማሪው(ዋ) ደህንነት እና የተማሪን ስኬታማነት ለመደገፍ አስፈላጊ የሆነ ሌላ የ MCPS ሠራተኛ ብቻ መረጃ የማጋራት ውስንነት አለው። ከዚህ በተጨማሪ፣ በህግ ከተጠየቀ መረጃ መስጠት አለበት። ካልሆነ ግን፣ ውይይት የተደረገባቸው ማቴሪያሎች በሙሉ በምስጢር ይቀመጣሉ።

የካውንስሊንግ ክፍለጊዜዎቹ ፊት-ለ-ፊት በአካል ወይም ቨርቹወል ይደረጋል። በቨርቹወል ካውንስሊንግ በጣም ጠቃሚ ነገሮች እና አስጊ ሁኔታዎችም ይኖራሉ (ለምሳሌ፡- ስለ ታማሚ ምስጢር ውስንነት) በአካል ከሚካሄደው ክፍለጊዜ የተለየ ሊሆን ይችላል። ለቨርቹወል የካውንስሊንግ አገልግሎቶችም ምስጥራዊነት ይጠበቃል፣ እና ከአንዱ ወገን ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር የትኛውም ወገን ክፍለጊዜውን ሪኮርድ አያደርግም። ቨርቹወል ካውንስሊንግ እንዲካሄድ ስምምነት ከተደረገ እንዴት መሠራት እንዳለበት የ MCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ ያብራራል-ታብራራለች። በቨርቹወል ክፍለጊዜ ተማሪው(ዋ) "webcam ወይም smartphone" መጠቀም ይኖርበ(ባ)ታል። ቨርቹወል ካውንስሊንግ በሚካሄድበት ክፍለጊዜ፣ ፀጥታ ያለበት ቦታ፣ ትኩረትን የማይረብሽ ነፃ የሆነ የግል ቦታ (ሞባይል ስልክ ወይም ሌሎች ዲቫይሶችን ጭምር)። ህዝብ የሚጠቀምበት/ነፃ Wi-Fi ከሚሆን ይልቅ አስተማማኝነት ያለው የኢንተርኔት ግንኙነት መጠቀም ይመረጣል-ይመከራል። ቴክኒካል ችግሮች ቢያጋጥሙ ክፍለጊዜውን እንደገና ለመጀመር ወይም ሌላ የጊዜ ቀጠሮ ለመያዝ እንዲቻል (ለምሳሌ፡- ተማሪው(ዋ)ን ለማግኘት የሚያስችል የስልክ ቁጥር) የ MCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ የመጠባበቂያ እቅድ ያዘጋጃል-ታዘጋጃለች። ድንገተኛ አስቸጋሪ ሁኔታ ለሚፈጠርበት ጊዜ፣ የ MCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ ቢያንስ አንድ የድንገተኛ-አስቸኳይ ጊዜ መገኘት ያለበ(ባ)ት ሰው እና ለአካባቢው አቅራቢያ የድንገተኛ ክፍል ጭምር የሚገልጽ የደህንነት እቅድ "safety plan" ይፈልጋል-ትፈልጋለች። የ MCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት፣ ካውንስሊንግ በአግባብ ካልተከናወነ ክፍለጊዜዎቹን በአካል በመገኘት መካሄድ እንደሚያስፈልግ ይወስናል-ትወስናለች።

ይህ የምክር አገልግሎት የማግኘት ስምምነት መግለጫ ቅጽ ለአንድ የት/ቤት አመት/ዘመን ያገለግላል። ተማሪ በካውንስሊንግ አገልግሎት መሣተፍ በራስ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም በላይ በተማሪው(ዋ) ወላጅ(ጆች)/ሞግዚት(ቶች) ወይም ብቃት ባለው-ባላት ተማሪ አማካይነት በማንኛውም ጊዜ ስምምነቱን ማቋረጥ ይቻላል። ወላጆች ስለ ልጃቸው መሻሻል ሁኔታ እንዲገለጽላቸው የትምህርት ቤትን ካውንስለር፣ ሳይኮሎጅስት፣ ወይም ሶሻል ዎርከር እንዲያገኙ-እንዲያነጋግሩ-እንዲጠይቁ ይበረታታሉ።

የእርስዎ ልጅ በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆን-እንድትሆን ድጋፍ ስለሚሰጡ እናመሰግናለን።

☐ እኔ-- ______________________ የግል ካውንስሊንግ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ/እንድታገኝ ፈቃድ ሰጥቻለሁ።
(የተማሪው/ዋ ስም)

☐ እኔ ለ ______________________ የግል ካውንስሊንግ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ/እንድታገኝ ፈቃድ አልሰጠሁም።
(የተማሪው/ዋ ስም)

ወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው-ያላት ተማሪ ስም (ይጻፉ) ______________________

ወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው-ያላት ተማሪ (ፊርማ) ______________________ ቀን_____/_____/______

የ MCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ ስም (ይጻፉ) ______________________

የ MCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ (ፊርማ) ______________________ ቀ_____/_____/______

የ MCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ የስልክ ቁጥር______-______-_______ እና ኢ-ሜይል ______________________

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት እባክዎ ለተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት-Office of Student and Family Support and Engagement (OSFSE)፣ በስልክ ቁጥር 240-740-5630 ይደውሉ። የእርስዎ ልጅ በትምህርት ቤት ስኬታማ እንዲሆን-እንድትሆን ድጋፍ ስለሚሰጡ እናመሰግናለን።

ስርጭት፡- 1/MCPS Counseling Provider-ለMCPS ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጪ፣ 2/Student Confidential File-ለተማሪ ምስጢራዊ ፋይል፣
3/Parent/Guardian/Eligible Student-ለወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው-ያላት ተማሪ